# በ 19 ዓመቴ ወልጄው ጠፍቶ ሞቷል ያልኩትን ልጄን አገኘሁት!!!

ፍቅሬ ቶለሳ ጅግሳ (ዶ/ር)

ውድ አንባብያን ሆይ፣ የምሥራች! የምሥራች ስላችሁም በሃገራችን ባሕል አጸፋውን "ምስር ብላ!" በሉኝ:: ልቤን ወደሰማይ እያዘለለ፣ እግሮቼን ጮቤ የሚያስመታ ነገር ሰሞኑን ገጥሞኛልና:: እሱውም፣ ከ አያሌ ከዘመናት በፊት ዕድሜዬ 19 ሳለ የወለድኩት ልጄ፣ ያውም የበሁር ልጄ፣ ጠፍቶብኝ "በቃ፣ ሞቷል፣ ተከቷል!" ብዬ እርሜን አውጥቼ እያዘንኩ እኖር ነበር:: በቅርቡ ግን፣ ያን ሞቷል፣ ወድሟል ያልኩትን ልጄን ባልጠበቅሁት ሁኔታ አግኝቼው በደስታ እየተምነሸነሽኩ እገኛለሁ:: የኔን ልጆች ሁሉ የምትወዱ ወዳጆቼ እንግዲህ ከ እኔ ጋራ ፈንጥዙልኝ! በወዳጅ ደስታ የማይፈነጥዝ የለምና::

ዳሩ ግን "የቡህር ልጄ" እና "ልጆቼ" ስላችሁ፣ እውነት ከሥጋዬ አብራክ የተውለዱ ልጆቼ እንዳይመስሏችሁ:: ከመንፈሴ፣ ከመንፈሴም ጠልቀው ከነፍሴ ስለተወለዱት ልጆቼ ነው የማወጋችሁ:: ግጥሞቼን ማለቴ ነው:: ምን ማለቴ እንደሆን ተረዳችሁልኝ?

የ 19 ዓመት ልጅ ሳለሁ አንድ ትልቅ ግጥም ደርሼ ነበር:: ታሪኩም እንደዚህ ነው::--
በዛንዘመን፣ እውቅ ጋዜጠኛና የልብ-ወለድ ደራሲ የነበረው ብርሃኑ ዘርይሁን የ *አዲስ ዘመን* ጋዜጣ አዘጋጅ ነበር:: በዚህም ምክንያት፣ በአንድ ወቅት ላይ የተለያዩ ርዕሶችን ለአንባቢዎች እየሰጠ በየሳምንቱ በድፍን ኢትዮጵያ የግጥም ውድድር ያኪያሄድ ነበር:: ከሳምንታቱ በአንደኛው ላይ "ዕምቦቃቅላው ሕፃን" በሚል ርዕስ እንጽፍ ዘንድ አንባብያኑን ጋበዘን:: እኔ በዛን ጊዜ በድሬደዋ የልዑል መኮንን ሁለተኛ ደረጃ ተምህርት ቤት በ 12ኛ ክፍል የምማር የ 19 ዓመት ልጅ ነበርኩ:: ርዕሱን ለቀም አድርጌ "ዕምቦቃቅላው ሕፃን" ብዬ ምንም ሳልቸገር ግጥሙን አውርጄ ጽፌ ለጋዜጠኛው ሰደድኩለት:: የውድድሩን ውጤት ዜና በናፍቆት ስጠባበቅ ለምን ከመላው ኢትዮጵያ ተወዳዳሪዎች በሞላ እንደኛ እልወጣላችሁም መሰላችሁ? በዚህ ምስራች ደስ ሲለኝ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ወሽመጤ ተቆመጠ!-- "ግጥሙ አንደኛ ቢወጣም በመርዘሙ ሳይታተም ቀርቷል፤" ሲል አቶ ብርሃኑ ዘርይሁን ሆዬ አፈነው! ከዛ በኋላ የግጥሙ ደጋግሞ አንባቢ እኔው ብቻ ሆንኳ:: በዛን ጊዜ ደጋግሜ ስለአነበብኩት በወቅቱ በቃሌ ይገኘው ነበር:: ከዛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን አጠናቅቄ ለ አንደ ዓመት ስኮላርሺፕ አግኝቼ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ አመራሁና ስመለስ እቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ይኒቨርሲቲ ገባሁ:: በዚያን ዓመት ይመስለኛል ግጥሙን ባልሳሳት ስሙ አቶ ጌታቸው ለሚባል *ፀደይ* የተሰኘ አዲስ የግል መጽሄት ለሚያዘጋጅ ሰው እንዲያትመው የሰጠሁት:: ግጥሙ መታተም አለመታተሙን ሳልከታተል ቀርቼ ከዛ በኋላ በቃ ረሳሁት::

የዛሬ 33 ዓመት በጀርመን ሃገር የ ዶክትሬት ተማሪ ሳለሁ፣ አንዲት ግጥሞቼን የምትወድ ልጅ "ዕምቦቃቅላው ሕፃን " የተሰኘውን ግጥሜን *ፀደይ* መጽሄት ላይ ድሮ ኢትዮጵያ ሳለች እንደ አነበበችና መጽሄቱም እነሱ ቤት እድደሚገኝ አበሰረች:: ካዛ በኋላ ልጅቱን አላገኘኋትም::

በአዲስ አበባ ከተማ በ አንድ ቤተመጻህፍት ውስጥ የምትሠራ አንዲት እህትን በቅርቡ ግጥሙን በፀደይ መጽሔት ላይ በየቤተመጻህፍቱ እንድትፈልግልኝ ለመንኳት:: እሷም እጅግ ቁምነገረኛ ኢትዮጵያዊት በመሆኗ፣ ግጥሙ ከገባበት ገብታ አገኘችልኝ:: ለዚች "ፍቅር ዳዊት" ለተባለችው ወጣት በዚህ አጋጣሚ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

በርግጥም ግጥሙ የበሁር ልጄ ነው:: በልጅነቴ ከጻፍኳቸው ግጥሞቼ እሱ ዋና ነው፣ ብዬ ስለማስብ:: አሁን መለስ ብዬ የግጥሙን ጥልቀት ሳጤነው፣ ከዕድሜዬ በላይ ነውና:: ግጥሙ ዝም ብሎ ተራ ግጥም ሳይሆን ፍልስፍናን ያንፀባርቃልና:: እሁን እንደገና መላልሼ ሳነበው "እውነት በ 19 ዓመት ዕድሜዬ ጻፍኩትን?" ብዬ ሳልደመም አልቀረሁም:: በአብዮቱ ውስጥ ወይም በስደት እንደሞቱት ጓደኞቼ ሞቼ ቢሆን ኖሮ፣ ይሄ ግጥም ከእኔ ጋራ ተቀብሮ በነበር:: አንጋፋዎቹ ገጣሚዎቻችን ዕድሜያቸው በአስራዎቹ ውስጥ (ልጆች ሳሉ) የገጠሙዋቸው ግጥሞች ከነበሩ ታትመው አላገኘናቸውም:: በርግጥም ሁሉም ማለት ይቻላል ግጥም መድረስ የጀመሩት ከአደጉ በኋላ ነበር:: ስለዚህ የልጅነታቸውን ሥራዎች ታተመው ባናገኛቸው አይደንቀንም:: እኔ ይሄ ነገር ገና በልጅነቴ ስለገባኝ ከ 16 ዓመቴ እስከ 23 ዓመቴ የገጠምኳቸውን አጠራቅሜአቸው፣ የ ዛሬ 42 ዓመት የ*መነን* መፅሄት አዘጋጅ የነበረው ደራሲው ስብሃት ገብረእግዚአብሄር ሊያትማቸው ፈልጎ፣ ሁሉንም አስረከብኩትና የደራሲነት ትምህርት ለመማር የዛሬ 40 ዓመት ወደ መስኮብ አገር አመራሁ:: አቶ ስብሃት ግጥሞቼን የት እንዳደረሳቸው በ ወጣቱ ገጣሚ በ ታገል ሠይፉ የዛሬ 17 ዓመት ባስጠይቀው "አብዮቱ በፈነዳ ጊዜ መላውን ቢሮ ቀበሌ ስላሸገው የፍቅሬም ግጥሞች አብረው ታሽገው ይሆናል፤" ሲል መለሰ:: ከማዘን በቀር ምንም ማድረግ አልቻልኩም:: እንደ አጋጣሚ ሆኖ ታላቅ ወንድሜ ከቀበሌ ብዝበዛና ፍተሻ እያንቆራጠጠ ያዳነልኝን የማስታወሻ ደብተሮቼን እና ቁርጥራጭ ጽሁፎቼን የዛሬ አስራዐምስት ዓመት ኢትዮጵያ ሄጄ ሳለሁ ስለአስታቀፈኝ የተወሰኑት ተርፈውልኛል:: ከ 18 ዓመቴ ጀምሮ አትዮጵያን እስከለቀቅኩበት ጊዜ ድረስ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ላይ በአዘጋጁ በ አቶ ከበደ አኒሣ መልካም ፍቃድ በርካታ ግጥሞቼ ለንባብ በቅተው ስለነበር ለወደፊቱ ከአንዱ የኢትዮጵያ ቤተመጻህፍት እንደማገኛቸው እምነቴ ነው:: ለነገሩማ ገጣሚውና ጸሃፌ-ተውኔቱ አቶ መንግሥቱ ለማም ግጥሞቼን በጣም ይወዷቸው ስለነበር፣ ከጋዜጣ ቆርጠው እያወጡ

ያጠራቀሚቻቸውን አንድ ጊዜ ሳያሳዩኝ አልቀሩም፡፡ በንጉሡ ዘመን ቋንቋ አካዳሚ እየሠሩ የኢትዮጵያ ደራሲያን ዋና ፀሃፊ በነበሩበት ወቅት፡፡ የእሳቸው የግል ወይም የሥራ  ማሕደር የት እንዳለ ባውቅ ኖሮ እዛ ውስጥ ግጥሞቼን በፈለግኳቸው ነበር፡፡  የሆነ ሆኖ፣  እጄ ውስጥ ያሉትን እና ሌሎቹንም አፈላልጌ  እግዚአብሄር ዕድሜ ከሰጠኝ ለወደፊቱ አሳትማቸዋለሁ፡፡

ይህን "ዕምቦቃቅላው ሕፃን" የተሰኘውን ግጥም  ምንም ያለ ችግር ከልቤ አፍልቄ በ 19 ዓመቴ ብደርሰውም፣ ግጥሙን ከመድረሴ በፊት እዚህ ላይ መደበቅ የማይገባኝን አንድ ቅድመ-ዝግጅት አንዳደረግሁ መግለጽ ይገባኛል፡፡-- የ እዚህኑ ግጥም ሃሳብ እና ስሜት ከሁለት ዓመታት ቀደም ብዬ፣ ማለትም በ 17 ዓመቴ በ እንግሊዝኛንቋንቋ ደርሼ በትምህርት ቤቱ መጽሄት ላይ አሳትሜው ነበር፡፡ ወዲያውኑም ግጥሙን ያነበቡት አርመኖች፣ አሜሪካኖችና ሕንዶች አስተማሪዎቼ ከበውኝ  "አንተ ትንሽ ልጅ ነህ፡፡ ይህን የመሰለ የበሰለ የሕይወት ፍልስፍና እና አንድ ሽማግሌ የሚሰማውን ስሜት እንደምን ልታውቅ ቻልክ?" በማለት በመገረም ጠይቀውኝ ነበር፡፡ እኔም "ይህን ሳወቅ የቻልኩት ገጣሚ ስለሆንኩ ነው፡፡" ብዬ መለስኩላቸው፣ "ገጣሚ ማለት ከፍተኛ የምናብ ኃይል ያለው ሰው ነው፡፡ ለምሳሌ እኔ ጨረቃ ላይ ወጥቼ አላውቅም፡፡ ሆኖም በምናቤ ኃይል ወደ ጨረቃ ተጉዤ ጨረቃ ላይ ስለ አሉ ነገሮች ልጽፍ እችላለሁ፡፡" ከመምህራኖቼ ውስጥ በዕድሜውም ሆነ በ እንግሊዝኛ ስነጽሁፍ ጥልቀቱ የታፈረውና የተመሰገነው ሕንዳዊው ሚስተር ስታሊ የምንለው አረጋዊ፣ ወደ መምህራኑ ዞሮ *"ፍቅሬ ቶለሳ አንድ ቀን ስሙ የተጠራ ገጣሚ ይሆናል!" ሲል ተናገረ፡፡*

ዳግም ውድ አንባብያን፣ በተለይም የኔን ግጥሞች የምታፈቅሩትና ለመረዳትም የምትጥሩት ሆይ! እነሆ የልጅነት የበሁር ሥራዬ፡፡ አሁን የደረስኩበትን የሥነግጥሜን ደረጃ ስትመረምሩ የተነሳሁበትንም ታስተውሉ ዘንድ "ዕምቦቃቅላው ሕፃን" ያግዛችኋል ብዬ አምናለሁ፡፡ ለምሳሌ አሁን ስገጥም፣ ከዚህ በፊት እንደ አወጅኩት ቤት የምመታባቸው ቃላት የአማርኛ ቋንቋ እስከፈቀደልኝ ድረስ በሁለት ወይም ሶስት ፊደላት ይመታሉ፡፡ በዚህ በ "ዕንቦቃቅላው ሕፃን" በተሰኘው ግጥም ላይም አንዳንዴ የዚህ ዐይነት አመታት ይንጸባረቃል፡፡ ለአብነት ያህል በዚሁ ግጥም ውስጥ "መሰጠው" ብዬ በ "ሰጠው፡ እገጥማለሁ፡፡ "አምሮለት" ብዬ "ሰምሮለት" ደግሞም "ቅን" ብዬ "ወርቅን"፣ "ሽብሽቦ" ብዬ "ሽቦ" "ጥቁር፡ ብዬ "ቁር" ስል እመታለሁ፡፡ ዛሬ የምጽፋቸው ግጥሞች ዘጠና በመቶ የዚህ ውስጣዊ ባህሪ አላቸው፡፡ ሥለዚህም የኔ ልዩ መለያ አሻራዬ ሆነዋል፡፡ ከእንግዲህ በስንፍና ወደ ኋላ የማልመለስበት ደረጃ ላይ ደርሻለሁና፡፡ ግጥሙን እንደ አለ ከ *ፀደይ መፅሔት* ወስጄ ከትቤዋለሁ፡፡ ያስተካከልኩት ባብዛኛው ታይፐ መቺዋ እና ምናልባትም አራሚው የገደፉትን ወይም የዘለሉዋቸውን ስንኞችና ቃላት መጨመሬ ነው፡፡ የግጥሙን ስንኞችና ቃላት የቅደም ተከተል አወራረድ ሁሉንም ባላስታውሰውም፣ አብዛኞዎቹ ቃላትና ስንኞች ባለፉት 45 ዓመታት እውስጤ ይዘምሩ ስለነበሩ በአታሚዎቹ ስህተት ከወሪጂናሌ ጽሁፌ ላይ በትክክልል ያልተገለበጡትን ሁሉ በቀላሉ ሳርማቸው ችያለሁ፡፡ ለማንኛውም ጠፍቶ የመገኘቱን የምስራች ወደ አበሰርኩላችሁ ወደ በሁር ልጄ ልመልሳችሁና ከእርሱ ጋራ ላስተዋውቃችሁ

# ዕምቦቃቅላው ሕፃን

(ፍቅሬ ቶለሳ)

መልሳ ቀልሳ ፀሐይ ስትጠልቅ፣
እየደጋገመች ስትወጣ ስትጠልቅ፣
ጨረቃ ስትታይ ስትጠፋ፣
አንዱ ቀን በሌላው ሲገደል፣ ሲገፋ፣
ወራት አንዱ ባንዱ በህብረት ተጣምረው፣
"ነፍስ" ፈጠሩና ሥጋና ደም አብረው፣
ጊዜው ረዘመና፣
"ልደት" ነው ተብሎ፣ "ሕይወት" "ሕልውና"
ዋይታ፣ ሆታ የሌላትን ፀተኛውን አገሩን ሲያጣ፣
የሕልም ዓለሙን ሲነጠቅ የሚደርስበትን ዕጣ፣

ሕይወት ጠመዝማዛ የሾህ መንገድ፣ መሆኑ ገብቶት ማለዳ፣
ገና በጠዋት ታይቶት፣ "ሰው" የመሰኘቱ ዕድል የሕልውናው ዕዳ፣
ብትንሽ አቅሙ ሊከላከል ሲጮህ፣ ሲያቀልጥ የ'ምቢታ እሪታ፣
ግንባሩ እስኪኮማተር፣ ላንቃው እስከምትደርቅ፣ ሢያሰማ አቤቱታ፣
በማይቋቋመው ረቂቅ ኃይል፣ ምስጢር በሞላው ግዙፍ ሥልጣን፣
ያለፍቃዱ ተጎትቶ፣ ወደዚህ ዓለም መጣ ዕምቦቃቅላው ሕፃን፡፡

ዓመት ባመት ተለውጦ፣
ዘመን በዘመን ተውጦ፣
ክረምት በክረምት ሞቶ፣
በጋ በበጋ ተከቶ፣
አንዱ ሲጠፋ ሌላው ታይቶ፣
እንዲያ፣ እንዲያ ሲባል ዘግይቶ፣
የሕጻንነት ጊዜው በንኖ፣
የ'ንቅልፍ ሕይወቱ ተንኖ፣
ተኝቶ ከነበረበት የሕልም ዓለም በከባድ ሰመመን ተውጦ፣
ዕምቦቃቅላው ማሞ ነቅቶ፣ ዙሪያውን ዐየ በተመስጦ::

የሕዋዉ ምጥቀት፣
የዘመናት ርቀት፣
የተራሮች ቁመት፣
የመንገዶች ርዝመት፣
ሊያስጠፋው የማይችል ትዝታውን ከቶ፣
ልጅነት መጥቶለት፣ ህፃንነት ቀርቶ፣
ዙሪያው ጣዕም ሰጠው፣
የጠዋት መንፈሱን ተፈጥሮ መሰጠው::
የነካው በእጁ፣
ወርቅ ሆነው ለልጁ::
ከፎለፎል ፀሐይ፣ ጥጥ ከሞላው ሰማይ፣ ከ'ምድር አክንባሎው፣
ከመሬት ኮከቦች ካበቦቹ ገጥሞ በመንፈስ ባካልም፣ አብሮ ሆነ ውሎው::

በድቅድቁ ጥልመት፣ ከጠቆረው ሕዋው እጅጉን እርቀው፣
በረቂቅ ባህር ላይ ተንሳፈው፣ እዛና እዚህ ታጭቀው፣
እያቆለቆሉ፣ ዐይን ዐይኑን የሚያዩት በቢጫው ዐይናቸው፣
እልፍአእላፉ ኳክብት፣ ወጉት በፍቅራቸው ምን ሳይሳናቸው::
ታዲያ ኑሮን መረቀ፣ ሕይወት ውብ ናት አለ፣
ለወግ እንዲበቃ፣ ቶሎ ቶሎ እንዲያድግ፣ እጅጉን ቸኮለ::

እንዲያ እንዲያ ሲባል ቆይቶ፣
አንዱ ሲጠፋ ሌላው ታይቶ፣
ክረምት በክረምት ሞቶ፣
በጋ በበጋ ተከቶ፣
ዓመት ባመት ተለውጦ፣
ዘመን በዘመን ተውጦ፣
በልጅነት እንቅልፍ ያየው ሕልም አምሮለት፣
የትናንቱ ሕፃን ምኞቱ ሰምሮለት፣
አደገ በታምር፤ ሽምበቆ ቁመቱ ከሰማይ ላይ ወጣ፣
ገላው ተራራ አክሎ ብዙ ለውጥ አመጣ::

ዳሩ ባንዲት አፍታ፣
ያዘው ፈጠነና የመምሰል በሽታ፣
ጭለማው ብርሃንን፣ ብልጭልጩ ወርቅን፣
እሾሁም አበባ ፣ ክፉም ሆነለት ቅን::
ባፍንጫው የገባው፣ የጠለቀው ልቡ፣
ብርጉድ ሽቶ ሆነው፣ አስደሳች ለቀልቡ::

አሞቀው እሳቱ፣
ጣፈጠው እሬቱ፡፡

እንደ 'ሳት ገሞራ፣ እንደፈላ ወተት ልቡ ገነፈለ፣
ዘለለ ቀበጠ፣ የሚይዘው አጣ፣ ስሜቱ ሺ ቦታ ድንገት ተክፈለ፡፡

ቅብጠቱ እንደበዛ፣ ግለቱ እንዳየለ፣
አሁንም እንዲያ እንዲያ እያለ፣
ተፈጥሮ ሥርዓቱን ጠብቆ፣
የንቅስቃሴ ዑደቱን አጥብቆ፣
ፀሐይ መልሳ ቀልሳ ስትሰርቅ፣
ደጋግማ ስትወጣ ስትጠልቅ፣
ጨረቃ ስትታይ፣ ስትጠፋ፣
ጊዜ የሰጠው የዘመን ሸክላ እያለፋ
ጊዜ የጣለውን የዘመን ድንጋይ ሲገፋ፣
ከርሞ... አድሮ...
የትናቱ ጮርቃ ገጥታው እንዳይሆን ተቀያይሮ፣
“ዳዴ ቦሩ ገልና፣ ሽንብራህ ፈሰሰው፣
“እሽሩሩ ማሞ፣ ጠላትህ ያልቅሰው፤”
ይሉት የነበሩት ሕፃን ልጅ ሳለ ጥንት፣
ያኔ ያፈቀሩት ጎረቤት አዛውንት፣
አይተውት አለፉት ረስተው እንደዋዛ፣
እሳቸውም ጀጅተው፣ እሱም ተለዋውጦ ዘመኑ ቢበዛ፡፡

መለዋወጡን ግን አሁንም ቀጠለ፣
ከማስተዋል ወተት ጥቂት ተጎንጭቶ፣ አእምሮው በሰለ፡፡
ናላው በጥያቄ መታጨቅ ጀመረ፤
በሰሜን በደቡብ፣ በምዕራብ፣ በምስራቅ እየጠረጠረ፣

ትክ! ባለው ዐይኑ፣ ዙሪያውን እያየ በነጋ በጠባ፣
“ስለምን? እንደምን? ኧረ ምን?!” ይል ገባ፡፡

በጥያቄ ጋራ ሲወጣ ሲወርደው፣
ስሜቱ ተዳፍኖ፣ ሰውነቱ ዝሎ ከቅብጠት ሲያግደው፣
ግማሽ መልስ አግኝቶ ራሱን ነቀነቀ፣
ሕይወትንም አውቆ በእምባ ታነቀ፡፡

ሲታዘብ ቆይቶ፣
ሁኔታውን ዐይቶ፣
“ስማኝ ምክሬን” አለው “ይልቅ እረፍና”
ሕሊናው መለሰ፣ ሠጠው ፍልስፍና--
“ሾሁ አበባ ነው፣ ልቦናን ካላሉት፣
“መራራን በጣፋጭ ሲያውቁ ካልመሰሉት፣
“ሆን ብለው ካላሉት ጭለማውን ብርሃን፣
“ሆድን ካልደለሉት ልብ ቢያውቅም እንኳን፣
“ሕይወት አያመችም፣ አይገፋም ኑሮ፣
“ ካልተዉ ማየትን ነገርን አጥቁሮ፡፡”

ይህን ፍልስፍና፣ በተመስጦ አድምጦ፣ መርምሮ ነገሩን፣
ተከትሎት ሄዶ፣ አዋለው በግብር የሕሊና ምክሩን::
እናም ሁለንተናው፣
በእውነትም ቀናው::
ዘሎ ፈነደቀ፣
በፍንጥዝ ወደቀ፣
እልልታው ቀለጠ፣
ዓለምን ጨበጠ፣
እስክስታ ወረደ፣
ተቅበጥብጦ አበደ::

ልማደኛ ፀሐይ ሳትሰለች ስትሠርቅ፣
ጨረቃም ቁልቁል እየታዘበች፣ ስትወጣ ስትጠልቅ፣
ዓመት ባመት ተለውጦ፣
ዘመን በዘመን ተውጦ፣
ክረምት በክረምት ሞቶ፣
በጋ በጋ ተከቶ፣
አሮጌው ሲወድም አዲሱ ደርቶ፣
ደካማው ሲያፍር፣ ጎብዙ ኮርቶ፣

ዕምቦቃቅላው ሕፃን ሙሉ ሰው ተብሎ፣ እድሜው ገፋፋና፣
ባእምሮው ምድጃ ተዳፍኖ የነበር፣ ቀድሞ የለኮሰው የትዝታ ፋና፣
ጊዜን ንፋስ አርጎ ዳግም ብው! ብሎ፣
ያነደው ጀመረ ውስጥውስጡን አቃጥሎ፣

ረቂቅና ግዙፍ ባሕሪው አንዱ ሌላውን ሲሞግድ፣
ረቂቁ "እኔ ላይል!" ግዙፉ "እኔ በልጬህ ላግድ!"
በማለት ሲዋጉ እሱን መሃል ከተው፣
ነፍሱ ተጨነቀች… ካንዳቸውም ሳይሆን ጨነቀው፣ ታከተው::
ሃሳብ ጨመደደው፣
ትካዜ አሳበደው፣
ጥርጣሬ ያዘው፣
ይሉኝታ መረዘው፣
ጥንቃቄ አበዛ፣
በሃዘን ተገዛ::
ፈንጠዝያ ወዳጅ፣ ተጫዋች ነበረ፣
ያሁሉ ጠባዩ አሁን ተቀበረ::

ጭር ባለ ሌሊት፣ ቁጭ ብሎ ሲያድር 'ራሱን እየያዘ፣
ልቅሶ ሆነ ሥራው፣ ከሰውነት ወጣ፣ በቁሙ ፈዘዘ::
ጥቁር ሆነ ጥቁር፣
ቁርም ሆነ ያው ቁር፣
ሾህ በሾህነቱ፣
ረጋ መሰረቱ
ቀረ አበባነቱ::
ብልጭልጩን ሁሉ ወርቅ ነው ማለትን፣
ሕሊና አልሰማ አለ፣ ልብ አላምን አለ የማይሆን ተረትን::

ተንግዲህ በኋላ ነገር ተበላሸ፣
የኑሮ ቅመሙ የመምሰል በሽታው፣ ጥሎት ታገር ሸሸ፡፡
ዙሪያው ሲኦል ብቻ፣ ሕይወት ገሃነም ሆነች፣
የቅጽበት ፍስሃ፣ እንደጢስ በነነች፡፡

ጥሎ እንድይጥል ሆኖ፣
ብዚህ ጭለማ ውስጥ ሳለ ተጨፍኖ፣
የጥልመት ማሷን ጧፍ፣
የዚን ዓለም ድጋፍ፣
መንፈስን አፋፊን፣
ባየር ተንሳፋፊን
የኮከብ ስባሪን
በሰማይ በራሪን፣
ጅራታሚን ኮከብ፣ የጠዋት ጤዛዋን፣
ኳ! ብልጭ! ባይዋን፣
ያችን መብረቅ ዐይነት፣ አጋጠመው ተስፋን፣
ያችን ቦግ! ድርግም! ያች በናኝ አረፋን፡፡

ሌላውን ረገመ፣ ሁሉን አወገዘ፣
ተስፋና ምኞትን እንቅ አርጎ ያዘ፡፡
በልሙ የሚያየውን፣
ለማድረግ የእውን፣
መለስ እንኳን ሳይል ተቻኩሎ ወደፊት፣
ሄደ ገሰገሰ፣ በረረ ያለ እርፌት፡፡
በዚህ ግስጋሴው፣ ምንም እንኳ ባይኖር ያተረፈው ነገር፣
የህልውና ሽክም ቅልል አለውና፣ ተወ ማንገራገር፡፡

ታዲያ ዓመት ባመት ተለውጦ፣
ዘመን በዘመን ተውጦ፣
ክረምት በክረምት ሞቶ፣
በጋ በበጋ ተከቶ፣
ተፈጥሮ ስርዓቱን ጠብቆ፣
የ'ንቅስቃሴ ዑደቱን አጥብቆ፣
ኖሮ፣ ከርሞ... ኖሮ... ኖሮ...
ማንኛውም ነገር ተቀያይሮ፣
'ራሱ ጥጥ መሰለ!!! ፊቱ ጨመደደ!!! ግንባሩም ሸብሸቦ፣
ዐይኖቹ ተዳክመው፣ ከወገቡ ጎብጦ፣ ይርገፈገፍ ጀመር እንድ ስልክ ሽቦ፡፡

በራሪው ዘመኑ የት እንደከነፈ፣
ያ ጥላማው ዕድሜው እንዴት እንዳለፈ፣
ምኑንም ሳያውቀው፣
እምባው እንዳነቀው፣
ሕፃኑ ልጅ ጃጀ!!!!!!!
እንደዋዛ አረጀ!!!!!!!!

ባየችው ጉድ እየሳቀች ፀሃይ ስትሰርቅ፣
ጨረቃ እየታዘበች ስትወጣ ስትጠልቅ፣

ክረምት በክረምት ሞቶ፣
በጋ በበጋ ተከቶ፣
አልፋኦሜጋዊው ዑደት ቀጥሎ፣
አሁንም ከርሞ፣ አሁንም ውሎ፣
በተፈጥሮ መለዋወጥ ቀን ተቆጥሮ፣
በጸሃይ መውጣት መግባት ዘመን ተቀምሮ፣
ባልተረጋጠ ስሌት በግምት፣ ቅጽበቱ ወቅት ተብሎ ድሮ፣
ሕፃኑ ልጅ ቢታይ አድጎ ተጨማዶ፣
ሽማግሌ ተሰኝቶ፣ መሠረቱ ተክዶ፣
አንገቱን እንደሰበረ፣
ወደመሬት እንዳቀረቀረ፣
እንደዋዛ እንደ ቀልድ ቀረ።

ይሉኝታ ይዞት ሲቸር ሲፈራ፣
ድፍረት ሲያጣ፣ ድፍረት ሲያፈራ፣
ሒዶት ከነበረው የሕይወት ዘመንን እንደጉዞ ቆጥሮ፣
ከልጅነት ቀዬው መጣ ተመልሶ፣ ጳመና ይመስል የትም ዞሮዞሮ።
አካባቢን ቃኝቶ፣ ባይኖቹ ጭጋግ ውስጥ ቀዩን አድማስ ርቆ፣
ወድህኋላም በትካዝ ሰማያት አቋርጦ፣ በትዝታ ፈረስ ሰማንያ ዓመት ዘልቆ፣
አሁን የጠፋውን፣ የያኔውን ራሱን አትኩሮ አስተዋለ።
ሕፃን ማሙሽ ሆኖ ድቅ! ድቅ! እያለ፣
ካበቦቹ መሃል፣ ከሰማዩ በታች ፀሃይዋ ጮራ ውስጥ፣
ከኮከቦቹ ጋር፣ የጠቆረው ሌሊት ስሜቱን ሲመስጥ፣
አስታውሶ የጥንቱን፣
ትክ! ብሎ ሲቃኝ ከዋክብት፣ እጽዋቱን፣
እንደልጅነቱ እነሱ ያው ናቸው፣
ውበታቸው ያው ነው፣ ቁመታቸውም ያው እንዲሁም ጎናቸው።
በሱ ላይ ብቻ ነው ጊዜ የቀለደ፣ ዘመን ያሾፈበት፣
ቦታው እንዳለ ነው፣ ሕፃኑ ብቻ ነው ሰዓት ያለፈበት።

ይህን ጉድ ማስተዋል፣ አላስችል ስላለው ተወና ፈጽሞ፣
ወደፊት ቢያማትር፣ ጊዜን አልፎ ቀድሞ፣
ፊቱ ተደቅኖ ድቅድቅ ጥልመት ዐየ!!!
ቀለጠና ልቡ፣ እምባውን አፍሶ፣ ከዚያ ቦታ ሄደ ምንም አልዘገየ!!!

*እንደ ኤውሮፓውያን አቆጣጠር በ 1968 ዓመተ ምሕረት፣ በድሬደዋ ከተማ የተገጠመ።*

**ገጣሚው ዶ/ር ፍቅሬ ቶለሳ ጂግሳ፣ በ lulu.com or amazon.com ላይ የሚገኘው የ**
The Hidden and Untold History of the Jewish People and Ethiopians, ደራሲ ነው። አስተያየት ሊለግሱት ለሚሹ እሱ የሚገኝበት ኢሜል fiktolo@gmail.com ነው። *ክራር እየመታ ያዋሃዳቸው ወረጅናሌ ግጥሞቹና ዜማዎቹ በቅርቡ በ ሲዲ ይወጣሉ።*